ቁጥር - DFAG-F D6.4/2/19
ቀን- 29/7/2012

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለክብርት ዶ/ር ምስራቅ መኮንን
በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የፓርላማ ፅ/ቤት ኃላፊና የዲላ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ ሰብሳቢ
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>የዲላ ዩኒቨርሲቲ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርትን ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል፣</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን ዩኒቨርሲቲ የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 2 ገጽ የሂሣብ መግለጫዎች በድምሩ 11 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከማክበር ሰላምታ ጋር!

ወርቅአፈራሁ ወንድሙ
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ፣</u>

- **ለዲላ ዩኒቨርሲቲ** (ከ9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፣ 47 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች እና 19 ገጽ አባሪ ጋር)
  <u>ዲላ ፣</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ዲላ ዩኒቨርሲቲ

የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የዲላ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል:: የሂሳብ ሪፖርቱ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ

ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡ ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የዲላ ዩኒቨርሲቲ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ዩኒቨርሲቲው ዘላቂነት ባላቸውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ ማለትም የተማሪዎች ምግብ ቤት መስተንግዶና ጽዳት፣ ረዳት የኤሌክትሪክ ባለሞያ፣ የግብርና ተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ ሰራተኞች እና የኦዳአያ ግቢ ካምፓስ ፖሊስ ሰራተኛ በቋሚነት ቀጥሮ ማሰራት ሲገባው በቀን ሰራተኝነት በመቅጠር በድምሩ ብር 957,187.00 ክፍያ ተፈፅሞ መገኘቱ፣

2. በጤና ሳይንስ ኮሌጅ በሆስፒታሉ የተገዙት እቃዎች/አገልግሎቶች/በናሙና ከተመረጡት ውስጥ የኤጀንሲው የአቅራቢነት ሰርተፊኬት የሌላቸው፣ የገበያ ጥናት ያልቀረበባቸው ግዥዎች እንዲሁም ጥራቱ ሳይረጋገጥ በአጠቃላይ ድምር የብር 2,579,471.54 በጨረታ መፈጸም የነበረበትን ግገር በመከፋፈል በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የተፈጸመ መሆኑ፣
3. የሼልፍ ግዥ በዋጋ ማወዳደሪያ ለመፈጸም የተለያዩ ድርጅቶች ቀርበው ጥረት የእንጨትና ብረታ ብረት ማህበር በዋጋ ማቅረቢያ ደረሰኙ ያቀረበው ዋጋ ተ.እ.ታ ያካተተ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን ባቀረበው ዋጋ መሰረት ብር 65,447.00 ዝቅተኛ ቢሆንም ተ.እ.ታ. እንዳልተካተተ ተደርጎ ድጋሚ የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲሰላ በመደረጉ ብር 78,400.00 ከነተ.እ.ታ. ያቀረበው እንዲያሸንፍ በመደረጉ ብር 12,953.00 ዩኒቨርስቲው አለአግባብ የከፈለ መሆኑ ፣
4. በቀን 06/05/11 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 813007 ከተፈራ ታምራት ሱፐር ማርኬት መኮረኒ እና ድንች ግዥ ብር 163,521.71 በካሽ ሴልስ አታችመንት፣ በቀን 30/12/10 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 751512 አልሳም ኃላ/የተ/የግ/ማ ብር 383,660.02 በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ክፍያ **በድምሩ ብር 547,181.73** ገንዘቡ መከፈሉን ለማረጋገጥ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ወይም የካሽ ሬጂስተር ደረሰኝ ሳይቀርብ ሂሳቡ በዱቤ እና አታችመንት ደረሰኝ አላግባብ የተወራረደ መሆኑ፣
5. በቀን 29/10/2011 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 69545 በሂሳብ መደብ 6223 ለዳርጌ ፀጋዬ ለምርምር በቅድሚያ ክፍያ ለተሰጣቸው ሂሳብ ለማወራረጃነት የቀረበው ሰነድ ለተለያዩ ግለሰቦች በቀን ከብር 123 እስከ 300 ለአንድ ወር በድምሩ ብር 165,500፣ ለሁለት ግለሰቦች በቀን ብር 123 ለ7 ወር በድምሩ ብር 103,320.00 ውል የተገባ ቢሆንም
   - ከተወራረደው ሂሳብ ውስጥ በውሉ መሰረት ለሁለት ግለሰቦች በቀን ብር 123 ለ7 ወር ብር 51,660.00 ተከፍሎ

መወራረድ ሲገባ ብር 51,660.00 ከተገባው ውል በላይ ተከፍሎ መገኘቱ፣

- በቀን 30/10/2011 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 36093 በሂሳብ መደብ 6256 ብር 69,000.00 ያለማስረጃ የተወራረደ መሆኑን፣

በድምሩ ብር 120,660.00 በቂ ማስረጃ ሳይቀርብ የተወራረደ መሆኑ

6. **በጊዜ** ገደቡ መወራረድ ሲገባው በድምሩ ብር **3,741,749.92 በወቅቱ** ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩ፣
7. በጊዜ ገደቡ መከፈል ሲገባው **በድምሩ ብር 6,823,698.37** በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ መኖሩ ፣

ከላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች በስተቀር የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ትክክለኛውን ገጽታ ያሳያሉ፡፡

1. <u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች(Emphasis of Matters)</u>

1.1 ከጤና ሳይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታል ከኮሌጁ ፋይናንስ ክፍል 12 መምህራን ለት/ት ሄደው በወቅቱ ያልተመለሱ በመሆኑ የሚፈለግባቸው ብር 4,543,044.49፣ 12 መምህራን የሚፈለግባቸው የብር መጠን ያልተገለጸ ነገር ግን የውላቸው ማብቂያ ከ2006 እስከ 2010 ሲሆን ከሰው ሀ/ሥ/አ/ዳይሬክቶሬት በውል መሰረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ለህግ አገልግሎት የቀረበ ቢሆንም ክስ ለመመስረቱ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ

2. ሌሎች ጉዳዮች(Other Matters)

2.1.1 በዩኒቨርስቲው በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች ለግንባታ ግዥ ክፍያ ሲፈጸም በባንክ በኩል ለመፈጸሙ ለማረጋገጥ የሚያስችል የባንክ አድቫይስ ተያይዞ ሳይቀርብ በቼክ ክፍያ መፈጸሙ

2.1.2 በዲላ ዩኒቨርሲቲ ከአዲስ ራዕይ እንጀራ አቅራቢ፣ በርሱ ፈቃድ እንጀራ አቅራቢ፣ ማቱንቴ እንጀራ አቅራቢዎች ጋር ጤፍና ሌሎች አስፈላጊ ግባቶች እንደሚያቀርብና ማህበሩ በሚፈለገው ጥራት እንጀራ ማቅረብ የሚል ሲሆን ምንያህል ጤፍ ቀርቦላቸው ምንያህል እንጀራ እንደሚያቀርቡ በግልጽ በውሉ ላይ ያልተገለጸ መሆኑን እንዲሁም የውል ማራዘሚያ በሚል ለረጅም ዓመታት ከተገለጹት አቅራቢዎች ብቻ ግገር የሚከናወን መሆኑ

2.1.3 የውስጥ ኦዲት የሰው ኃይልን በተመለከተ፤

- በዩኒቨርሲቲው የሰው ኃይል መዋቅር መሠረት 15 የኦዲት ባለሙያዎች የሚያስፈልግ ሲሆን በአሁን ሠዓት 8 የኦዲት ባለሙያዎች ሲኖሩ ከዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት የሰው ኃይል መዋቅር ጋር ሲነፃፀር 7 የኦዲት ባለሙያዎች በቅጥር ያልተሟሉ መሆኑን
- የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት የማያዘጋጅ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

2.1.4 ተያዥ ሳይኖራቸው ስለተቀጠሩ ሠራተኞች ሁኔታ በተመለከተ፤

ረሺድ ጀማል በቀን 01/06/2002 ዓ.ም ወ/ሮ አበባ ገ/መድህን በቀን 01/11/2008 ዓ.ም በዲላ ዩኒቨርስቲ ዋና ገቢ በግዥ ሰራተኛ ሆነው የተመደቡ ሲሆን ምንም አይነት ዋስትና ወይም ተያዥ ያላቀረቡ መሆኑ፣

2.2 ንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ፣

2.2.1 የቋሚና አላቂ ዕቃ ንብረት በተመለከተ

የንብረት ማከማቻ ለብዙ ዓመት ያለ ስራ(አገልግሎት) ሳይሰጡ የተቀመጡ ለሆስፒታል የሚጠቅሙ ትልቅ Pure Water Machine ፣ 3 Lotzener strasse 2-4D-28207 bremen Germany፣ ካልኩሌተር በቁጥር 26፣ 2 ትልቅ ኮፒ ማሽን፣ ፍራሽ 165፣ የተቀመጡ መኖራቸውን፣

➢ **የመለዋወጫ ዕቃ የንብረት ማከማቻ**

የንብረት ማከማቻ ክፍሉ ሰፊ እና በቂ ቢሆንም ንብረቶችን በምቹ ሁኔታ ለማስቀመጥ የሚረዳ ቢሆንም በክፍሉ አቧራ መኖሩና የጽዳት ችግር መኖሩ፤ ከ1993 ጀምሮ ከትምህርት ሚኒስትር መጡ የተባሉ ለመኪና ጥገና አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ የቶዮታ፣ ኒሳን፣ ታታ እና ማርቼዲስ መገኘቱን፤ በአላቂ ዕቃ ንብረት ክፍልና እስፔር ፓርት የንብረት ክፍል የሚሰራ አንድ ሰዉ መሆኑ፤

➢ **የተሽከርካሪ መለዋወጫ ንብረት መጋዘን በሚመለከት**

ንብረቱን፣ ንብረት ገቢ እና ወጪ ሰነዶች በአንድ ሰራተኛ ነው የሚያዙት፣ ንብረት መጋዘኑ ንብረቶችን ለመደርደር የሚያስችል መደርደሪያ ወይም ሼልፍ በበቂ ሁኔታ ባለመኖሩ ንብረቶች ተቀላቅለው ነው የሚገኙት፣ ንብረቶቹ ገቢ እና ወጪ ለመቆጣጠር የሚረዳ ስቶክ ካርድ ሆነ ቢንካርድ አለመዘጋጀቱን ለማየት ተችሏል፡፡

➢ **ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች ማከማቻ መጋዘን**

በዋናው ግቢ፡-

የተማሪዎች የምግብ ማከማቻ መጋዘኖች በግዥ ከአቅራቢዎች የሚቀርቡት ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ ህህሎችና ቁሳቁሶች ስቶክ ካርድ እና ቢንካርድ

የሌለ መሆኑ፡፡ በተማሪዎች ምግብና ንብረት ማከማቻ መጋዘን ውስጥ በሞ/19 ገቢ የሆኑ መኮረኒ 3,600 ኪ.ግ.፣ ምስር 4,000 ኪ.ግ.፣ ፓስታ 5,000 ኪ.ግ.፣ ዘይት 11,647.8 ኪ.ግ.፣ ተቀምጠዉ በመጋዘን ውስጥ መገኘቱ፡፡

➢ **በጤና ሳይንስ ኮሌጅ የንብረት ማከማቻ መጋዘን ይመለከታል**

ንብረቶችና ቢንካርድ ያላቸው ንብረቶችም ቢሆኑ ከካርዳቸው ጋር የማይመሳሰሉ ንብረቶች የሚገኙ መሆኑን፣ ይህውም በጣም ብዙ የቆዩ ለብልሽት ሊዳረጉ በሚችሉ መልክ የተቀመጡ መሆኑን

➢ **በጤና ሳይንስ ኮሌጅ የህክም አቅርቦቶች፣ መድኃኒቶችና መሳሪያዎች መጋዘኖች በተመለከተ፤**

የህክናምና መድኃኒት መጋዘን እና መሳሪያዎች መጋዘን ቢንካርድ የሚጠቀሙ ሲሆን ስቶክ ካርድ፣ ወይም ዘመናዊ ሶፍትዌር በመጠቀም በአግባቡ እና በወቅቱ ለመመዝገብ የሚረዱ አሰራሮችን የማይጠቀሙ መሆኑን፣ የፕሮግራም መድኃኒቶች አብዛኛው ዋጋቸው የማይታወቅ መሆኑን በተጨማሪ የመድኃኒት አገልግሎት አሰጣጥ አግባብነት እንዲሁም መጋዘኖቹ የውስጥ ኦዲትና የጥራት ቁጥጥር ኮሚቴ ጋር ኦዲት መደረግ ቢኖርበትም ኦዲት እንዳልተደረገ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የተሽከርካሪ አያያዝና የጀኔሬተር ነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ፤

ተሽካርካሪዎች አያያዝና የጀኔሬተር ነዳጅ አጠቃቀም በዚህ አግባብ ስለመያዛቸው ኦዲት ሲደረግ፡-

- ሰሌዳ ቁጥር 4-00244 ሚትስቡሽ ፒካፕ, 4-0711 ሞተር ሳይክል, ከደህ ወደ ኢት ያልዞሩ መሆኑን
- በተቋሙ የአሽከርካሪዎች ልዩ መታወቂያ ያልተዘጋጀ መሆኑን፣

- እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በኪ.ሜ. የሚጠቀመውን ነዳጅ ለማወቅ የሚያስችል ጥናት (Normalization) ያልተከናወነ መሆኑን፣
- የተሽከርካሪዎች ኪሎ ሜትር መቁጠሪያ የማይሰሩ መሆኑ
- ለጀኔሬተር የዋለ ነዳጅ ፍጆታ ኦዲት ሲደረግ ዋናው ግቢ፣ አዳኢያ ግቢ፣ ሆስፒታል ግቢ፣ ባዮ ጋዝ፣ ችግኝ ጣቢያ፣ መኖሪያ ግቢ፣ የሚገኙ 6 ጀኔሬተሮች አጠቃላይ ጥገናና ኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት ቁጥጥር እንደሚደረግባቸው የተገለጸልን ሲሆን አጠቃላይ ጥገናና ኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት አገልግሎት ለጀኔሬተሮቹ የሚያስፈልገውን ነዳጅ ከሚመለከተው አካል በደብዳቤ ሲጠይቅ ቀድቶ እንደሚያስረክቡ በዚህም 151,241.00 በሊትር በ2011 በጀት ዓመት እንደተጠቀሙ የተገለጸ ሲሆን ከዛ ባለፈ ነዳጁ በትክክል ለታለመለት አገልግሎት ስለመዋሉ፣ በሰዓት ወይም በቀን የሚያስፈልገው የነዳጅ መጠን ጥናት ያልተደረገ፣ መጠኑ ያልተወሰነና የመቆጣጠሪያ ስልት የሌለ መሆኑን፤

2.3 <u>በ2010 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸውን ግኝቶች በተመለከተ</u>፤

- ከሁለት ዓመት በላይ ከሆናቸው የህንድ መምህራን ብር 1,548,196.71 የሥራ ግብር ግብር ሳይቀነስ ለውጭ ሃገር መምህራኖች ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ከሄዱት ይርጎለም አበበ ደመወዝ ብር 10,470.00 ከ01/11/09 - 30/03/10 የ5 ወር ግማሽ ደመወዝ ብር **26,175.00** መከፈል ሲገባ ሙሉ ደመወዝ ብር 52,350.00 በመከፈሉ አላግባብ ብር **26,175.10** የተከፈለ መሆኑ፤
- ቤት ለተሰጣቸው መምህራን በድጋሚ የቤት አበል ብር 31,400.00 የተከፈላቸው መሆኑ፤
- የዩኒቨርሲቲው ሆስፒታል በየወሩ ለቶፕ አፕ በማለት ከብር 300.00—8,640.00 በማድረግ ብር 1,981,386.80 እና ለኦቨር ሎድ በማለት ከብር 3,333.00 —

7,200.00 በማድረግ ብር 3,336,051.70 በጠቅላላ ድምር ብር 5,317,438.53 በበጀት ዓመቱ ከመደበኛ በጀት ከደመወዝ ጋር ተካቶ የተከፈለ መሆኑ፤

- ደመወዝ በ160 ሰዓት ተካፍሎ እና ውጤቱ በተሰራበት የሥራ ሰዓት ተባዝቶ ለአስተዳደር ሠራተኞች ብር 1,500,236.68 በብልጫ የተከፈላቸው መሆኑን፤

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት

መጋቢት 2012 ዓ.ም